# በደቡብ ወሎ ዞን ለጋምቦ ወረዳ በደረሰ የትራፊክ አደጋ የ38 ሰዎች ህይወት አለፈ።



መጋቢት 4 2010 ዓ.ም. ደቡብ ወሎ ዞን ለጋምቦ ወረዳ የደረሰና የ38 ሰዎች የሞቱበት የትራፊክ አደጋ

በደቡብ ወሎ ዞን ለጋምቦ ወረዳ ትናንት መጋቢት 4/2010 ዓ/ም በደረሰ የትራፊክ አደጋ የ38 ሰዎች ህይወት አለፈ፡፡ 10 ሰዎች ከባድና ቀላል አደጋ ደርሶባቸዋል፡፡
የህዝብ ማመላለሻ አውቶቡሱ 48 ሰዎችን አሳፍሮ ለጋምቦ ወረዳ ቀበሌ 07 -ልዩ ስሙ ገነቴ ሰላምበር በተባለ ልዩ ቦታ ላይ 5 ሜትር ቁልቁለት ላይ ዘሎ በመግባቱ ነው አደጋው የደረሰው።
አደጋው ከመካነ ሰላም ተነስቶ ወደ ደሴ 48 ሰዎችን አሳፍሮ ሲጓዝ በነበረ የህዝብ ማመላለሻ አውቶብስ ተሽከርካሪ ላይ ነው የደረሰው።
የህዝብ ማመላለሻ አውቶብሱ በለጋምቦ ወረዳ ከገነቴ ከተማ በቅርብ ርቀት አቧራ ጥግ የሚባለውን ጠመዝማዛ መንገድ እንደጨረሰ መንገዱን ስቶ በመውደቁ ነው አደጋው የደረሰው።
ተጎጅዎቹ በአቀስታ ህዳር 11 እና በደሴ ሪፈራል ሆስፒታሎች የሕክምና እርዳታ እየተደረገላቸው ነው።
እግዚአብሔር በደረሰው አደጋ ህይወታቸውን ያጡትን ወገኖቻችን ነብስ ይማር። በዚህ አደጋ ቤተሰቦቻቸውን ላጡ ወገኖቻችን መጽንናትን እንመኛለን።



መጋቢት 4 2010 ዓ.ም. ደቡብ ወሎ ዞን ለጋምቦ ወረዳ የደረሰና የ38 ሰዎች የሞቱበት የትራፊክ አደጋ



መጋቢት 4 2010 ዓ.ም. ደቡብ ወሎ ዞን ለጋምቦ ወረዳ የደረሰና የ38 ሰዎች የሞቱበት የትራፊክ አደጋ